የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት

የሰ/መ/ቁጥር 239841
መጋቢት 28 ቀን 2015 ዓ/ም

ዳኞች፡- አበባ እምቢአለ

ብርሃኑ አመነው

በእወቅቱ በላይ

ቀነዓ ቂጣታ

ኑረዲን ከድር

አመልካች፡- ጆይቴክ ኃ/የተ/የግ/ማ.- ጠ/ሻምበል ተሾመ ደምሴ ቀረቡ

ተጠሪ፡- አቶ ገዙ ደግፌ- ቀረቡ

መዝገቡ የተቀጠረው ለምርመራ ሲሆን በዚሁ አግባብ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

የሰበር አቤቱታው ሊቀርብ የቻለው አመልካች ጥር 01 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ባቀረበው የሰበር አቤቱታ የቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ.ቁ.21358 በ19/03/2015 ዓ.ም የሠጠውን ውሳኔ የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ.ቁ.70213 በ11/04/2015 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.420740 በ27/04/2015 ዓም በሰጡት ትዕዛዝ ማጽናታቸው መሰረታዊ የሕግ አተረጓጎም ስህተት የተፈጸመበት በመሆኑ ሊታረም ይገባል በማለት ስላመለከተ ሲሆን አመልካች በስር ፍርድ ቤት ተከሳሽ ሆኖ ተጠሪ ደግሞ ከሳሽ ሆነው በአሰሪና ሰራተኛ ህግ ጉዳይ ተከራክረዋል፡፡

ተጠሪ በቀን 10/09/2014 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ አቤቱታ በአመልካች ድርጅት ውስጥ ከየካቲት 24 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ኬሚካል አሲድ በአበባ ምርቶች ላይ በመርጨት የስራ መደብ ተቀጥረው ሲሰሩ የኬሚካል ስራን ከሚሰሩበት ፋብሪካ በአይናቸው ላይ ተረጭቶ በሁለቱም አይናቸው ላይ ጉዳት አድርሶ ጉዳቱም በህክምና ቦርድ ውሳኔ መሰረት ከአጠቃላይ አካላቸው 72% መሆኑን እና አይናቸውም መስራት እንደማይችል መረጋገጡን መሰረት በማድረግ አመልካች ከስራ በ13/12/2013 ዓም ጀምሮ ያሰናበታቸው መሆኑን በመጥቀስ እድሜያቸው 25 ዓመት ሆኖ አማካኝ የመኖር እድሜያቸው 60

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ዓመት መሆኑን በማመልከት በወር ገቢያቸው ብር 2,815.00 በማስላት የ35 ዓመት በድምሩ ብር 1,182,300.00 በፍ/ብ/ህ/ቁ፣2123፣2090፣እና 2091 መሰረት ፣የህክምና ወጪ ያወጣሁትና እያወጣሁት ያለውን በድምሩ ብር 90,000.00 እንዲከፈለኝ፣ለወደፊት የማወጣው የህክምና ወጪ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 እና በፍታብሄር ህጉ መሰረት እንዲከፈለኝ እንዲሁም የሞራል ካሳ ብር 10,000.00 እንዲከፈለኝ ይወሰንልኝ በማለት አመልክተዋል፡፡

አመልካች በሰጠው መልስም ተጠሪ ክሱ በ14/07/2013 ዓም ሆኖ ክሱ የቀረበው ግንቦት 10 ቀን 2014 ዓም በመሆኑ ክሱ በአዋጁ አንቀፅ 163(3)እና (4) መሰረት ክሱ በይርጋ የታገደ ነው፣ተጠሪ ሰራተኛ በመሆኑ ክሱን ማቅረብ ያለበት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 እንጂ በፍ/ብሄር ህጉ መሰረት ሊሆን አይገባም፣ተጠሪ በአዋጁ አንቀፅ 109(4) ክፍያን ወስደው ክሱን ማቅረባቸው አግባብ አይደለም በማለት የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ያቀረበ ሲሆን በፍሬ ጉዳዩ ላይም በሰጠው መልስም የተጠሪ ደመወዝ ብር 840.00 እንጂ ብር 2090.00 አይደለም፣ለተጠሪ ኢትዮ ላይፍ ኢንሹራንስ ብር 66,960.00 በአመልካች ብር 51,042.59 በድምሩ ብር 118,002.00 የተከፈላቸው በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ፍርድ ቤቱም የአመልካችን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ በብይን ውድቅ አድርጎ በፍሬ ጉዳዩ ላይ በሰጠው ውሳኔም በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 96 መሰረት ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ የአሰሪውን ሀላፊነት መወጣት አለመወጣት መሰረት አድርጎ ከፈለገ በአዋጁ መሰረት አልያም በፍትሐ ብሄር ህጉ መሰረት የካሳ ክፍያ መጠየቅ የሚችል መሆኑ ስለተመለከተ ክሱ በፍትሐ ብሄር ህጉ መሰረት መቅረቡ አግባብ መሆኑን በመነሻነት በመጥቀስ በተጠሪ ላይ የደረሰው የስራ ጉዳት 72% መሆኑ በህክምና ቦርድ ስለተረጋገጠ የወር ገቢያቸው ብር 1,901.00 መሆኑ ከቢሾፍቱ ገቢዎች ባለስልጣን ስለተጣራ ለተጠሪ ሊከፈላቸው ከሚገባው በድምሩ ብር 574,862.40 ውስጥ በአመልካች የተከፈላቸው ብር 118,002.59 ሲቀነስ ብር 456,859.81 ስለሚመጣ ይህንኑ ገንዘብ አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል፣የተጠሪ የሞራል ካሳና የህክምና ወጪ ክፍያ ጥያቄ የህግና የማስረጃ ድጋፍ ስለሌለው ተቀባይነት የለውም በማለት ውድቅ አድርጎታል፡፡ይህ ውሳኔ ጉዳዩን በይግባኝ በተመለከተው የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤትና በክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ፀንቷል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር ተሰኝቶ ባቀረበው ሰበር አቤቱታም በተጠሪ አይናቸው ላይ ለደረሰው ጉዳት በአዋጅ ቁ.11562011 አንቀፅ 96(1) እና 109(4)(ሀ) መሰረት የጉዳት ካሳ ብር 118,002.59 የከፈለ ሲሆን አንድ ሰራተኛ የፍትሐ ብሄር ህጉን መሰረት አድርጎ የጉዳት ካሳ መጠየቅ የሚችለው በአዋጁ አንቀፅ 96(3) እና በሰ/መ/ቁ.80343 መሰረት ጉዳቱ በአሰሪው ጥፋት የደረሰ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ሆኖ እያለ ተጠሪ ክሱን ሲያቀርቡ በአሰሪዬ ጥፋት ጉዳት ደረሰብኝ በማለት ያቀረቡት ክስ በሌለበት እና በተጠሪ ላይ ለደረሰው ጉዳት አመልካች ድርጅት ጥፋተኛ ባልተባለበት ሁኔታ የስር ፍርድ ቤት አንድ ሰራተኛ በስራ ላይ ለደረሰበት ጉዳት በአማራጭ ከፈለገ በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ

ከፈለገ ደግሞ በፍትሐ ብሄር ህጉ መሰረት ሊጠይቅ ይችላል በማለት ውሳኔ መስጠቱ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት በመሆኑ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔ ይሻርልኝ በማለት አመልክቷል፡፡

አመልካች በተጠሪ ላይ ለደረሰባቸው ጉዳት በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 የተመለከተውን ካሳ እስከከፈለ ድረስ ጉዳቱ የደረሰው በአመልካች ጥፋት ነው ባልተባለበት ከውል ውጭ ካሳ ክፈል የመባሉን አግባብነት ለማጣራት የሰበር አቤቱታው ያስቀርባል ከተባለ በኋላ ለተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው ባቀረቡት መልስም አመልካች በደረሰብኝ ጉዳት ምክንያት ለህክምና ብር 100,000.00 በተለያየ መንገድ የሰጠኝ ሲሆን በዚህ ገንዘብም በተለያዩ የህክምና ተቋማት የታከምኩ ሲሆን ከአራት ጊዜ በላይ ቀዶ ህክምና የተሰራልኝ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በተሰጠኝ የህክምና ምርመራ ውጤት ጉዳቴ 85% መሆኑን የሚያሳይ በመሆኑ ይህም በደረሰብኝ ጉዳት አይኔ ሙሉ ለሙሉ ከጥቅም ውጪ ወደመሆን መድረሱን የሚያሳይ በመሆኑ ጉዳቱ የደረሰብኝ በህላፊው ትዕዛዝ ሳያስጠነቅቁኝ ሰራተኛው ሞተር እንዲያስነሳ እና እንዲመታኝ በማድረግ በአሰሪው ጥፋት ለመሆኑ በስር ፍርድ ቤት ገልጬ የተከራከርኩ በመሆኑ አመልካችም ይህንን ክዶ ያልተከራከረ በመሆኑ እንዳመነ የሚያስቆጥር በመሆኑ፣ይህንን ክርክርም በሰበር ደረጃ አንስቶ መከራከሩ አግባብነት ስለሌለው አመልካች እስክድን ድረስ ሊያስክመኝ የሚገባ ቢሆንም ከላይ ከተጠቀሰው ገንዘብ ውጪ ሰጥቶኝ የማያውቅ በመሆኑ ለምኜ እየታከምኩ በመሆኑ፣አመልካች በአዋጁ አንቀፅ 108 መሰረት ተገቢውን ክፍያም ያልከፈለኝ በመሆኑ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ሊፀና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

አመልካች የመልስ መልሱን በማቅረብ ክርክሩን አጠናክሯል፡፡

ከዚህ በላይ አጠር ባለመልኩ የተገለጸዉ የግራ ቀኙን ክርክርና በስር ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ዉሳኔዎች ይዘት የሚመለከት ሲሆን እኛም የሰበር አጣሪ ችሎት የያዘዉን ማስቀረቢያ ጭብጥ መሰረት በማድረግ በውሳኔው ላይ በዚህ ችሎት ደረጃ ሊታረም የሚችል የተፈጸመ መሰረታዊ የሕግ ስህተት መኖር አለመኖሩን አግባብነት ካለዉ ሕግ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለዉ መርምረናል፡፡በመሰረቱ ሰራተኛው ጉዳቱ የደረሰበት በስራ ላይ መሆኑ እስከተረጋጠ ድረስ አሰሪው ጥፋት ባይኖርበትም በስራ ላይ ሳለ ለሚደርሰበት ጉዳት ሀላፊ የሚሆን መሆኑ በአዋጅ ቁጥር 1156/2011 አንቀፅ 96(1) የተመለከተ ሲሆን ሀላፊነቱና የካሳው መጠን የሚወሰነውም በአዋጁ ከአንቀፅ 96 እስከ 112 በተመለከቱት ድንጋጌዎች አግባብ መሆኑን ከአንቀፅ 96(1) ድንጋጌ የምንረዳው ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ በሰራተኛው ላይ የስራ ላይ ጉዳቱ የደረሰው በአሰሪው ጥፋት መሆኑ ከተረጋገጠ በአንቀፅ 96-112 መሰረት ከሚረጋገጠውና ከሚከፈለው ክፍያ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ (ከውል ውጪ ባለ ሀላፊነት) ሰራተኛው አሰሪውን ካሳ የመጠየቅ መብት ያለው መሆኑን አንቀፅ 96(3) ያሳያል፡፡በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሰራተኛው አሰሪውን ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ በስር ፍርድ ቤት እንደተገለፀው ለሰራተኛው በነፃነት የተተወ መብት ሳይሆን ጥፋተኝነቱ ከተካደ የአሰሪውን ጥፋት በማረጋገጥ/አለማረጋገጥ ላይ የተመሰረተ መሆኑን ከድንጋጌው አጠቃላይ ይዘት የምንረዳው ነው፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ሰራተኛው በዚህ ድንጋጌ መሰረት ከውል ውጪ ባለ ሀላፊነት የሚገባውን ካሳ ሊያገኝ የሚችለው ከመነሻው በክሱ የስራ ላይ ጉዳቱ የደረሰበት በአሰሪው ጥፋት መሆኑን በመጥቀስ ክሱን አቅርቦ አሰሪው ጥፋቱን ካልካደ በእምነቱ መሰረት ከካደም በማስረጃ ጥፋተኝነቱን በማረጋገጥ ሊሆን ይገባል፡፡አሁን በያዝነው ጉዳይ ተጠሪ ለሰበር ክርክሩ በሰጡት መልስ በአመልካች ላይ በአዋጁ አንቀፅ 96(3) እና ከውል ውጪ ያለ ሀላፊነትን በሚደነግጉት የፍትሀ ብሄር ህጉ ድንጋጌዎች መሰረት ክሱን ሲያቀርቡ አደጋው የደረሰው በአሰሪው ጥፋት መሆኑን በግልፅ በማመልከት መሆኑን ጠቅሰው የተከራከሩ ቢሆንም ክሱን አስቀርበን እንደተመለከትነው አደጋው የደረሰው ሌላ ሰራተኛ የኬሚካል እቃውን በመንካቱ ምክንያት ኬሚካሉ አይናቸው ላይ በመረጨቱ መሆኑን በመጥቀስ ክስ ከማቅረባቸው ውጪ የስራ ላይ ጉዳቱ በአሰሪው ጥፋት የደረሰ መሆኑን ጠቅሰው ክስ ማቅረባቸውን አያሳይም፡፡የስራ ላይ ጉዳቱ የደረሰው በአሰሪው ጥፋት መሆኑ ተጠቅሶ ክስ ባልቀረበበት ደግሞ አመልካች ጥፋተኛ መሆኑን አምኗል የሚባልበትም አግባብ አይኖርም፡፡

በአጠቃላይ ተጠሪ በስር ፍርድ ቤት በአመልካች ላይ ክሱን ሲያቀርቡ የስራ ላይ ጉዳት የደረሰባቸው በአመልካች ጥፋት መሆኑን ገልፀው ባላቀረቡበት የስር ፍርድ ቤት በአሰሪና ሰራተኛ አዋጁ መሰረት አልያም ከውል ውጪ ያለ ሀላፊነትን በሚመለከቱት የፍትሐ ብሄር ድንጋጌዎች ክስ አቅርቦ የመጠየቅ መብቱ ለሰራተኛው የተሰጠ ምርጫ ነው በማለት ለህጉ የተሳሳተ ትርጉም በመስጠት በቀጣይ የክርክሩ ሂደትም አደጋው በተጠሪ አይን ላይ የደረሰው በአመልካች ጥፋት መሆኑ በተገቢው ማስረጃ ባልተረጋጠበት ብር 456,859.81 አመልካች ለተጠሪ ሊከፍል ይገባል በማለት መወሰኑ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ስላገኘነው ተከታዩን ወስነናል፡፡

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የቢሾፍቱ ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት በመ/ቁ.21358 በቀን 19/03/2015 ዓ.ም በዋለው ችሎት የሰጠው ውሳኔ እና ይህንን ውሳኔ በማፅናት የምስራቅ ሸዋ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.70213 በቀን 11/04/2015 ዓ.ም እንዲሁም የኦሮሚያ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ.420740 በ27/04/2015 ዓም በዋለው ችሎት የሰጡት ትዕዛዝ በፍ/ስ/ስ/ሕ/ቁ.348(1) መሰረት ተሸረዋል፡፡
2. በተጠሪ ላይ የስራ ላይ አደጋው በአመልካች ጥፋት የደረሰ መሆኑ በአመልካች የእምነት ቃል አልያም በተገቢው ማስረጃ ያልተረጋገጠ በመሆኑ የተጠሪ የካሳ ክፍያ ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ብለናል፡፡
3. ግራ ቀኙ በሰበር ክርክሩ ምክንያት ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡፡

<u>**ጉዳዩ ውሳኔ ስላገኘ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ይመለስ፡፡**</u>

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ወሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ት/በ

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም